# ፍኖተ ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ሚያዝያ 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 75


## “በህጋዊና ሰላማዊ የትግል ስልት የተለያዩ አስገዳጅ ተግባራትን ለመፈፀም ተዘጋጅተናል”

አቶ ሙላት ጣሰው የአንድነት ፓርቲ
የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ



የዚህም ድርጊት ፈፃሚ እራሱ ኢህአዴግ ሆን ብሎ ለስልጣኑ መራዘም የተጠቀመበት ኃላፊነት የጎደለው ስራ መሆኑንም የጥናት ውጤቶቻችን ያስረዳሉ። ይህንንም መሰረት በማድረግ አንድነት ዝም ብሎ መግለጫ ከማውጣት ባለፈ ወንጀለኞች በህግ እንዲጠየቁና መላው የሀገሪቱ ህዝብ በጉዳዩ ዙሪያ ተወያይቶ ውሳኔ እንዲያሳልፍ ከማድረግ በተጨማሪ በህዝብ ስም የዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶችና መንግስታት እንዲያውቁት ለማድረግ ልዩ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራ ለመግባት ዝግጅት ላይ ነን።

6

## መንግስት በጎንደር የበአል ቆዳ ለማሰባሰብ ያደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀረ

5

## የመድረክ ውህደትም ሆነ መፍረስ የአንድነት ቀዳሚ አጀንዳ አይደለም

አቶ ተክሌ በቀለ

8

## የፕሬስ ነጻነት ቀን በሀራምቤ ተከበረ

5

## መንግስት በህገ ወጥ እስር ቤቶችን ዜጎችን እያሰቃየ ነው

10

## በቡሌ ሆራ የሚትገኘው ቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን እንዲፈርስ መታዘዙ ቁጣን ቀሰቀሰ

10

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

ፍኖተነፃነት ጋዜጣሐምሌ2003ዓ.ምተመሰረተ፡፡

ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነው፡፡ ማንኛውም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው፡፡

## ርእሰ አንቀጽ

# በሽብርተኛነት ሰበብ ሀሳብን የመግለፅና የፕሬስ ነፃነትትን ማፈን ይቁም!

ባሳለፍነው ሳምንት ሚያዝያ 25 ቀን 2005 ዓ.ም የአለም ፕሬስ ነፃነት ቀን በአለም አቀፍ ደረጃ ተከብሯል፡፡ ይህ አለም አቀፍ የጋዜጠኞት በአል ከመከበሩ አንድ ቀን አስቀድሞ የፌደራሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ታዋቂው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና ሌሎች መሰል የህሊና እስረኞች ያቀረቡትን ይግባኝ ውድቅ አድርጎ ነበር፡፡

ከየአቅጣጫው የሚሰነዘሩ ውግዘቶችን "ጆሮ ዳባ ልበስ" ያለው ኢህአዴግ በችሎት በኩል ያንፀባረቀው የማንአለብኝነት ውሳኔ ፣ የፕሬስና ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት በአደባባይ ማፈኑን ቀጥሎበታል፡ ፡ ጋዜጠኞችን በማሸማቀቅ፣ በማሰደድና በማሰር ወደር ያልተገኘለት ኢትዮጵያን የሚገዛው ቡድንም መሰረታዊ የሰብአዊ መብት አካል የሆነው ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትን በአደባባይ ደፍጥጧል፡፡ የኢፌዴሪ ህገመንግስት ለመናገርና ለፕሬስ ነፃነቶች እንዲሁም ለሌሎቹም ሰብአዊ መብቶች ዋስትና ቢሰጥም መንግስት በተለያዩ ህገወጥ ህጎች ህገመንግስታዊውን ዋስትና በተግባር አፍኖታል፡፡ ህገመንግስታዊ ዋስትና የተሰጣቸውን የሰብአዊ መብቶች ፖለቲካዊ አንደምታ ባላቸው አዋጆች እየገደበ "ህገመንግስቱን" አስከባራለሁ የሚለው ኢህአዴግ፣ ህገመንግስተሰዊ መብታቸውን የተጠቀሙ ዜጎችን አስሮ "አሸባሪ" የሚል ታፔላ መለጠፉ ከአሁን በኋላ አያስኬድም፡ ፡ ምክንያቱም "አሸባሪ" የሚለው ቃል በየስርአቱ መዝገበቃላት የአገዛዙ ተቃዋሚ የሆኑትን እንጂ እውነተኞቹን አሸባሪዎች እንደማይመለከት በሀገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ግንዛቤ ተያዟልና፡፡ ለዚህ አባባል ማረጋገጫው ደግሞ ገዢው ቡድን አሸባሪ ብሎ ታፔላ የለጠፈባቸውን ዜጎች አለም አቀፉ ማህበረሰብ ተራ በተራ መሸለ ነው፡፡

የዘንድሮው የአለም የፕሬስ ቀን ሲከበርም የኢትዮጵያ መንግስት በሽብር ወንጀል የከሰሳቸው ጋዜጠኞች በአለም አቀፍ ተቋማት ተሸልመዋል፡፡ በሽብር ወንጀል ተፈርዶባት በቃሊቲ የምትገኘው ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት ሳይንስና የባህል ተቋም(UNESCO) የዘንድሮውን የጉዋሌርሞ ካኖ የአለም የፕሬስ ቀን ሽልማት ሰጥቷታል፡፡ በተመሳሳይ የሽብር ወንጀል ተከሶ የተፈረደበትና በስደት ሲውዲን ሚገኘው የቀድሞው የአዲስ ነገር ጋዜጣ ማኔጂንግ ኤዲተር ጋዜጠኛ መስፍን ነጋሽ፣ በቅርቡ የኢትዮጵያን መንግስት ይቅርታ ጠይቀው ከተፈቱት የሲውዲን ጋዜጠኞች ጋር በጋራ የሪፖርተርስ ዊዝ አውት ቦርደርስን (የሲውዲን ቅርንጫፍ) አመታዊ ሽልማት ተቀብሏል፡፡

ይህ ሽልማት የኢትዮጵያ መንግስት ሽብርተኝነትን ተገን በማድረግ በሀገር ውስጥ የሚካሄዱ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ለማዳፈን እያደረገ ያለው አፈና ያጋለጠ መሆኑን ብናውቅም፣ በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ለጉዳዩ በቂ ትኩረት ተሰጥቶታል ብለን አናምንም፡፡
አለም አቀፉ ማህበረሰብ በተለይም ረጂ ሀገራት የኢህአዴግ መንግስት የሚለግሱትን ገንዘብ በምን ላይ እንደሚያውለው በመከታተልና ለአፈና ተግባር እንዳያውለው በመቆጣጠር ረገድ በቂ ስራ አለመስራታቸው ለስርአቱ የልብ ልብ ተጥቶታል፡፡

የኢህአዴግ መንግስት ሀሳባቸውን ስለገለፁና በይፋ መንግስትን ስለተቹ ያሰራቸው ጋዜጠኞችና የፖለቲከኞች ካለግብራቸው በሽብርተኝነት መከሰሳቸው የስርአቱን አይን ያወጣ አምባገነንነትና አትንኩኝ ባይነት ያረጋገጠ ነው፡፡ ሆኖም ስርአቱ ሊገባው የሚገባው አንድ ሀቅ ህዝባዊ ተቃውሞንና ብሶትን ታጋዮችን በማሰር እንደማይቆም ነው፡፡

ዛሬም ኢህአዴግ ሀሳብን የመግለፅና የፕሬስ ነፃነትን እንዲያከብር፣ ሀሳባቸውን በመግለፃቸው ብቻ የታሰሩ ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ሙሉ ለሙሉ እንዲፈቱ እንጠይቃለን፡፡
ለመላው ኢትዮጵያዊም ሀሳብን የመግለፅና የፕሬስ ነፃነት ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ በመረዳትና መብት በትግል እንደሚገኝ በማመን የፕሬስና ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት እስኪረጋገጥ ድረስ በአንድነት እንታገል እንላለን፡፡

ጋዜጣችንን "ፍኖተ ነፃነት" ብለናታል "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር የነፃነት መንገድ ማለት ነው፡፡

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮችና አባላት አንዷለም አራጌን እንዳይጠይቁ በልዩ ሀይል ተባረሩ

የትንሳኤን በዓል ምክንያት በማድረግ ወጣቱን ፖለቲከኛና የፓርቲው አመራር አንዷለም አራጌን እንዲሁም ሌሎችን የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ለመጠየቅ ቅዳሜ መጋቢት 26 ቀን 2005 ዓ.ም የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮችና አባላት ቃሊቲ ቢሄዱም ለመጠየቅ እንዳይችሉ መደረጋቸውንና እስካፍንጫቸው በታጠቁ ልዩ ሃይሎች በግድ ከአካባቢው እንዲርቁ መደረጋቸውን የህዝብ ግንኙነት ክፍሉ አስታወቀ፡፡

እንደፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ገለፃ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወጣቱን ፖለቲከኛና ከፍተኛ አመራር አንዱአለም አራጌና ናትናኤል መኮንን ሽብርተኞች እንደሆኑና በሰላማዊ ትግል ሽፋን ሽብርተኝነትን እንደሚያራምዱ ተደርጎ የቀረበው ሀተታና ውሳኔ እጅግ ያሳዘናቸው በርካታ አመራሮችና አባላቱ በከፍተኛ መነሳሳትና ቁጭት ከ 20 በላይ የሚሆኑ የፓርቲው ሰዎች ከ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ እንኳን አደረሳችሁ ለማለት ቢገኙም የተሰጣቸው ምላሽ አንዷለምን ምግብ ከሚያመላልሱለት ጥቂት ቤተሰቦቹ ውጭ ማንም መግባት እንደማይችል ተገልፆላቸው በታጠቁ ሃይሎች ከአካባቢው እንዲርቁ ተደርገዋል ብሏል፡፡

በዕለቱ ቃሊቲ እስርቤት ለመጠየቅ ከተገኙት መካከል ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው፣ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ፣ ዶ/ር ያዕቆብ ሀይለማርያም፣ አቶ አክሉ ግርግሬ፣ አቶ ሙላት ጣሰው፣ አቶ ዘካሪያስ የማነብርሃን፣ አቶ ተክሌ በቀለ፣ አቶ ትዕግስቱ አወሉ፣ አቶ ዳንኤል ተፈራና ሌሎችም የፓርቲው አመራሮችና አባላት እንደተገኙ የህዝብ ግንኙነት ያደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

የማረሚያ ቤቱ የወቅቱ ተረኞች የስም ዝርዝራቸውን መታወቂያቸውን እያዩ ከተመዘገቡ በኋላ ከአቅማቸው በላይ እንደሆነ ገልጠው ወደ ዋናው የአስተዳደሩ የመግቢያ በር በመግባት ሃላፊዎችን እንዲያነጋግሩ ነግረዋቸው ወደዚያው በማምራት ቢጠይቁም እንዲጠብቁ ከነገሯቸው በኋላ የተሰጣቸው ምላሽ መጠየቅ አትችሉም የሚል ነው፡፡ ከዚህ በፊት በተለይ አንዷለም አራጌን ከጥቂት ቤተሰቦቹ በስተቀር ማንም እንዳይጠይቀው የተደረገ ሲሆን በተደጋጋሚ ቢያመለክትም ምንም ምላሽ ማግኘት አለመቻሉ ይታወቃል፡፡

ከዚህ በፊት ግን የበዓል ቀናት ብቻ የፓርቲው አመራሮችና የስራ ባልደረቦቹ ለተወሰኑ ደቂቃዎች በጅምላ እንዲጠይቁት ቢደረግም በዘንድሮው የትንሳዔ በዓል ግን የገጠማቸው በልዩ የታጠቁ ሃይሎች መባረር ሆኗል፡፡ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ አካባቢውን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ታጣቂዎች ወረውታል፡፡

ለመጠየቅ የመጡት መጠየቅ መብታቸው እንደሆነ ለማስረዳት ቢሞክሩም እነዚህ ሃይሎች መሳሪያቸውን በተጠንቀቅ በመያዝ ፀብ ለማስነሳት ሙከራ አድርገዋል በማለት የህዝብ ግንኙነት ክፍል ገልፆልናል፡፡

**በውጭ ሀገር ለምትገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል ለፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ የህትመት መሳሪያ ማደራጃ ለመግዛት እንዲቻል ጥሪ መቅረቡ ይታወሳል፡፡ በጥሪው መሰረት በርካታ ወገኖቻችን ተግባራዊ ምላሽ እየሰጡ መሆናቸው በወገኖቻችን እንድንኮራ አድርጎናል፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ ወገኖቻችን በገንዘብ አላላኩ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ በመጠየቃቸው ይህን ማብራሪያ አቅርበናል፡፡ ገንዘቡ የሚገባው በቀጥታ በፍኖተ ነጻነት አካውንት ነው፡፡**

1/በኦንላይን እርዳታ ለማድረግ ለምትፈልጉ በፔይፓል (pay pal secure payment)
እነዚህን ድህረ ገጾች ይጎብኙ

http://www.fnotenetsanet.com/
http://www.andinet.org/
http://www.andinetusa.org/

2/ በኤሌክትሮኒክስ ቀጥታ ለምታስተላልፉ

Andinet North America (Finote Netsanet News Paper)
Bank Name : Wells Fargo
ACC# 753-085-0978
Routing # 054-001-220

3/ በቼክ ወይም በገንዘብ ማዘዣ (money order)

Andenet North America (Finote Netsanet News Paper)
P.O.Box 48355
Washington DC 20002
Tel. (202) 462-0556 Fax: (202) 462-0557

ማሳሰቢያ ፡ ገንዘቡን ገቢ ካደረጋችሁ በሁዋላ በሚቀጥለው ኢሜይል አድራሻ ብታሳውቁን ለስራችን ጥራት ይረዳናል፡፡
Email: info@andinetusa.org
ስለትብብራችሁ አስቀድመን ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡
በመላው አለም የምትገኙ ወገኖቻችንም ይህን መረጃ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡

የፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ በሰሜን አሜሪካ

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
# UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

# የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሽብርተኝነት አይደለም!!!

## አሁንም የፖለቲካና የህሊና እስረኞች በአፋጣኝ እንዲፈቱ እንጠይቃለን!!!

## አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ(አንድነት)የተሰጠ መግለጫ

ፓርቲያችን አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) በሰላማዊና ህጋዊ የትግል መንገድ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፤ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንፈጥራለን፤ ስልጣንም በግለሰቦች ወይም በቡድኖች ይሁንታ የሚገኝ ሳይሆን በህዝቡ በልካም ፈቃድ ይሆናል የሚል ጠንካራ እምነት በመያዝ ከአምባገነኑ ስርዓት ጋር እየታገለ የሚገኝ ነው፡፡

ይሄ ጠንካራ የትግል መነሳሳታችን እና ያለን የህዝብ ድጋፍ ጠንካራ ተቃዋሚ በዓይኑ ማየት የማይፈልገው ገዥ ፓርቲ ጥርስ ውስጥ የከተተን በምስረታችን ማግስት ጀምሮ ነው፡፡ በርካታ አባሎቻችንንና አመራሮቻችንን ተልካሻ ምክንያት እየተለጠፈባቸው ታስረዋል፣ ተሳድደዋል፣ ተደብደበዋል፡፡

በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ ጠንካራ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችና ተቃውሞዎች ሁሉ የሚሰጣቸው ስም ሽብርተኝነት የሚል ነው፡፡ የስርዓቱ የስልጣን ማቆያ፣ የሀቀኛ ተቀናቃኞችና ስርዓቱን የሚተቹ ጋዜጠኞች ማሸማቀቂያ ብሎም ማስወገጃ መሳሪያ ሽብርተኝነት ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡

ፓርቲያችን አንድነትም ጠኒትና ማታ እየተጠቀሰ ዜጎች እንዲሸማቀቁ የሚደረግበትና የፖለቲካ አመራሮች የሚታሰሩበት የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ተቃውሞውን አሰምቷል፡፡ ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም የፀረ ሽብር ህጉ ገና ረቂቅ አዋጅ እንደነበረ ለማፈን እየተሰናዳ መሆኑን በመጥቀስ ‹‹የፀረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ አዋጅ በዜጎች ላይ ሽብር ፈጣሪ ነው›› በሚል ርዕስ ባወጣነው መግለጫችን ረቂቅ አዋጁ እንዳይፀድቅ የሚሰማ ባይኖርም አበክረን ጩኸታችንን አሰምተን ነበር፡፡

ወዲያው ህግ ሆኖ እንደወጣም የፀረ ሽብርተኝነት ትግልን ሽፋን በማደረግ የገዡው ፓርቲ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የማፈን ድብቅ ፍላጎት ተግባራዊ መሆን ጀመረ፡፡ የመጀመሪያው ሰለባ አንድነት ፓርቲ ነው ብንል ማጋነን አይደለም፡፡ አንዱአለም አራጌንና ናትናኤል መኮነንን የመሰሉ ከፍተኛ የፓርቲ አመራሮችንና ሌሎችን የፓርቲያችን አባሎች በእስር አጥተናል፡፡ እነዚህ በማናለብኝነት የሚፈፀሙ የገዡው ፓርቲ ሸፍጦች ትግላችንን የበለጠ የሚያጠናክሩና አፈናውን ለመስበር ጉልበት የሚሆኑን ናቸው እንጂ አንገታችንን አያስደፉንም፡፡ የፍትህ ተቋማት ላይ እምነት መጥፋቱ፣ ከላይ እስከታች ያለው የአፈና ቋንቋ ተመሳሳይ መሆኑና የገዡው ፓርቲ እጅ መርዘም ትግሉን ማፋፋምና አጠናክሮ መቀጠል ዋና መፍትሄ እንደሆነ የሚጠቁመን ነው፡፡

ሚያዚያ 24 ቀን 2005 ዓ.ም ይግባኝ ሰሚ ችሎት በነ አንዷለም አራጌ ፍርድ ላይ በአንድ መዝገብ ከተከሰሱት መካከል የአንዱን ጥቂት ዓመታት ከመቀነስ ባለፈ የስረኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ ትክክል ነው ብሏል፡፡ ይሄ ፍርድ የሚያስታውሰን የኪሊማንጃሮ ኢንተርናሽናል ኮርፖሬሽን ሊሚትድ በዓለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ ከፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር ይፋ ያደረገውን ጥናት ነው፡፡ በ27 የመንግስት ተቋማት ላይ በተደረገ ጥናት ‹‹በከፍተኛ ደረጃ የህዝብ አመኔታ ያጡ ተቋማት›› በሚል ርዕስ ስር በመጀመሪያ ደረጃ የተቀመጡት ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ ይሄ የሚያሳየው ፍ/ቤቶች የገዡው ፓርቲ ጉዳይ አስፈፃሚዎች እንጅ ገለልተኛ ተቋማት አለመሆናቸውን ነው፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወጣቱን ፖለቲከኛና ከፍተኛ አመራር አንዱአለም አራጌና ናትናኤል መኮንን ሽብርተኞች እንደሆኑና በሰላማዊ ትግል ሽፋን ሽብርተኝነትን እንሚያራምዱ ተደርጎ የቀረበው ሀተታ የፓርቲያችንን ጠንካራ መዋቅር ያላገናዘበ፣ የፓርቲያችንን መልካም ስም የሚያጎድፍ ነው፡፡ እነ አንዷለምም ሰላማዊ ታጋዮች እንጅ ሽብርተኞች አይደሉም፡፡ ሽብርተኝነት በኮሃራም ናይጀሪያ፣ በፓኪስታንና አፍጋኒስታን በየዕለቱ የምንሰማው እንጅ የኢትዮጵያ ችግር አይደለም፡፡

በአጠቃላይም የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉ የኢህአዴግ የዕድሜ ማራዘሚያና መጠቀሚያ ከመሆን በዘለለ ፋይዳ አለው ብለን አናምንም፡፡
የአመራሮቻችንንና አባሎቻችንን መታሰር አጥብቀን እንቃወማለን፡፡ አሁንም ደግመን ደጋግመን የምንለው በሽብርተኝነት ስም ዜጎችን ማሰር ይቁም፤ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሽብርተኝነት አይደለም፤ የፖለቲካና የህሊና እስረኞ በአስቸኳይ ይፈቱ፡፡
ትግላችን እስከለውጥ ድረስ ይቀጥላል!!!

### አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ(አንድነት)
### ሚያዝያ 25 ቀን 2005 ዓ.ም
### አዲስ አበባ

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# የፕሬስ ነጻነት ቀን በሀራምቤ ተከበረ





የአለም የፕሬስ ነጻነት ቀን በነፃ ጋዜጠኞች፣ ብሎገሮች፣አራማጆችና የፕሬስ ነፃነት ተቆርቋሪዎች በተገኙበት አዲስ አበባ በሚገኘው ሀራምቤ ሆቴል ተከበረ፡፡

በአሉን ለማክበር በማህበረሰብ ገጽ (በፌስ ቡክ ) አማካኝነት በተደረገው ጥሪ መሰረት የተሰባሰቡት ነፃ ጋዜጠኞች፣ ብሎገሮች፣አራማጆችና የፕሬስ ነፃነት ተቆርቋሪዎች በሀራምቤ ሆቴል በመገኘት ዕለቱን አክብረዋል፡፡ ‹‹የዘንድሮውን የፕሬስ ቀን የምናከብረው ታዋቂው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ያቀረበው የይግባኝ ጥያቄ ውድቅ በተደረገበት ማግስትና ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ የዩኔስኮን የአለም አቀፍ ሽልማት በወኪሏ አማካኝነት በምትቀበልበት ዕለት ነው›› ያለው አንድ ወጣት ጋዜጠኛ የሀገራችን ፕሬስ በተጋረጡበት ፈተናዎች ዙሪያ ውይይቱን አስጀምሯል፡፡

በዕለቱ ፕሬሱ በመንግስትና ራሳቸውን እንደ መንግስት በሚቆጥሩ ሃይሎች ከፍተኛ ጫና እየተደረገበት መሆኑን በመግለፅ ሰፊ ውይይት አድርገዋል፡፡ ተደራራቢ ጫና እየተደረገበት የሚገኘው ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትና መረጃ የማግኘት መብት አሁን ከሚገኝበት አስከፊ ሁኔታ በባሰ ረመጥ ውስጥ እንዳይገባ ጋዜጠኞች ሳይነጣጠሉ በአንድነት ጫናዎችን ለመቋቋም ተባብረው ለመስራት ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡

የበአሉ አከባበር ስነስርአት የተቋጨው በነፃ ጋዜጠኞች፣ ብሎገሮች፣አራማጆችና የፕሬስ ነፃነት ተቆርቋሪዎች ተከታታይ ውይይት ለማድረግ የሚያስችልና የሚያሰባስብ ማህበር የሚቋቋምበት ሁኔታ በጋራ እንዲጠና በመጠየቅ ነው፡
፡

# መንግስት በጎንደር የበአል ቆዳ ለማሰባሰብ ያደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀረ

ዛሬ በመላው ህዝበክርስቲያን ለተከበረው የፋሲካ በአል የታረዱ እንስሳትን ቆዳ “ለአባይ ግድብ” ማሰሪያ በሚል ጎንደር ከተማ መስተዳድር ለመሰብሰብ ያደረገው ሙከራ ሳይሳካ እንደቀረ የፍኖተ ነፃነት ምንጮች ከጎንደር ዘገቡ፡፡

በአንፃሩ የጎንደር ወጣቶች በከተማዋ ግንባታው በመካሄድ ላይ ላለው የሐዋርያው ዮሃንስ ህንፃ ቤተክርስቲያን ማጠናቀቂያ የሚውል በብዙ ሺዎች የሚቆጠር ቆዳ ማሰባሰባቸውን ምንጮቹ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ፍኖተ ነፃነት ምንጮች ዘገባ ቆዳ የመሰብሰብ ሙከራው ተደረገው የጎንደር ከተማ ከንቲባ በሰጡት ትዕዛዝ መሰረት ነው፡፡

ዘገባው እንደሚያስረዳው ህዝበ ክርስቲያኑ ለትንሳኤ በአል ያረዳቸውን እንስሳት ቆዳ ለአባይ እንዲሰጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የመንግስት አካላት ቤት ለቤት በመዞር ጥያቄ ቢያቀርቡም ከህብረተሰቡ ይሁንታ አላገኙም፡፡

የፍኖተ ነፃነት ምንጮች ያነጋገሯቸውና ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የጎንደር ከተማ ነዋሪዎች እንደተናገሩት ለሐዋርያው ዮሃንስ ህንፃ ቤተክርስቲያን ማጠናቀቂያ የቆዳ ልገሳ እንዲደረግ ህብረተሰቡ አስቀድሞ ተስማምቶ ነበር፡
፡ “መንግስት ከደሞዛችን ላይ ከበቂ በላይ የሆነ ገንዘብ ሰብስቧል፤ በበአል ሰዎች አሰማርቶ ቆዳ አምጡ ማለቱም አሳፋሪ ነው፡፡” ብለዋል፡፡

በከተማዋ ወጣቶች በተመራው ለቤተክርስቲያን ማሰሪያ የሚውለው የቆዳ ማሰባሰብ ተግባር ስኬታማ እንደነበር የዘገቡት ምንጮቻችን ህዝቡ አስቀድሞ በየአካባቢው ወኪሎችን በመሰየም ዝግጅት አድርጎ ነበር፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን የመንግስት ካድሬዎችም የትንሳኤ በአል የሚታረዱ እንስሳት ቆዳዎች ለአባይ ግድብ እንዲሰጡ ቅስቀሳ ሲያደርጉ የነበረ ቢሆንም ህዝቡ ለቤተክርስቲያን መስጠትን መርጧል፡፡

የኢህአዴግ መንግስት የአባይ ግድብን ስልጣኑን ለማስረዘም እየተጠቀመበት ነው የሚል ውግዘት እየደረሰበት መሆኑና በቅርብ ጊዜ ውስጥ በተለያዩ የአለም ክፍሎች ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን በቦንድ ሽያጭ ገቢለማሰባሰብ ያደረገው ሙከራ በተቃውሞ መክሸፉ ይታወሳል፡፡

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# “በህጋዊና ሰላማዊ የትግል ስልት የተለያዩ አስገዳጅ ተግባራትን ለመፈፀም ተዘጋጅተናል”

## አቶ ሙላት ጣሰው የአንድነት ፓርቲ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ



**የዛሬ እንግዳችን አቶ ሙላት ጣሰው ይባላሉ፡፡ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት) የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ሲሆኑ በአሁን ወቅት አንድነት ፓርቲ የዜጎችን መፈናቀል ያቋቋመው ልዩ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው፡፡ በዚህ ዙሪያ ከፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል፤ እንድታነቡ ጋብዘናል፡፡**

ፍኖተ ነፃነት፡- አንድነት በዜጎች መፈናቀል ዙሪያ ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ መዘጋጀቱ ተጠቁሟልና፤ ፓርቲው በዚህ ዙሪያ ምን እየሰራ ነው?

አቶ ሙላት፡- ፓርቲያችን በየትኛው አካባቢ የሚደረግ ዜጎችን የማፈናቀል ተግባር ህገወጥ መሆኑንና መቆም እንዳለበትም ከማንም ቀድሞ በተደጋገሚ መግለጫ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በፊት በጋምቤላ፣ በአፋርና በአንዳንድ ኦሮሚያ አካባቢ እንዲሁም በደቡብ ጉራፈርዳ ዜጎች ሲፈናቀሉ ተቃውሟችንን ብናሰማም የአቅም ውስንነት ስለነበር ወደስፍራው ወዲያው የፓርቲውን ልዑካን መላክ አልቻልንም ነበር ፡፡ ነገር ግን ሁኔታዎች ተባብሰው በመቀጠላቸው በቅርቡ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተፈናቀሉ የአማራ ተወላጅ ዜጎቻችን ላይ ፓርቲው የራሱን አጥኚ ወደ ስፍራው በመላክ ዝርዝር ሁኔታውን ለማወቅ ችለናል፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡- በጥናት ውጤቱ መሰረት ምን ተጨባጭ መረጃ አገኛችሁ?

አቶ ሙላት፡- ህዝባችን በታሪክ፣ በህግ፣ በደምና በባህል የተሳሰረ በመሆኑ መነጣጠል የሚቻል አይደለም፡፡ ነገር ግን በቅርቡ በዜጎች እርስ በርስ እንዳይተማመኑና አንድነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ እየተደረገው የማፈመናቀል ሂደት እጅግ የሚያሳዝና ተዘዋውረው የመስራት፣ ሃብት የማፍራትና የመጠቀም መብቶቻቸውንና በተፈጥሮ እና በህግ የተሰጣቸውን ፀጋና መብት ተነፍገዋል፡፡

በተለይ የአማራ ተወላጆች ላይ የተወሰደው የማፈናቀል ሂደት ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ላይ በማተኮራቸው ኢትዮጵያን ለመበታተንና ከሌሎች ወንድምና እህቶቹ ጋር ለማጣላት እየተደረገ ያለ ተግባር ነው ብለን መውሰድ እንችላለን፡፡

የዚህም ድርጊት ፈፃሚ እራሱ ኢህአዴግ ሆን ብሎ ለስልጣኑ መራዘም የተጠቀመበት ኃላፊነት የጎደለው ስራ መሆኑንም የጥናት ውጤቶቻችን ያስረዳሉ፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ አንድነት ዝም ብሎ መግለጫ ከማውጣት ባለፈ ወንጀለኞች በህግ እንዲጠየቁና መላው የሀገሪቱ ህዝብ በጉዳዩ ዙሪያ ተወያይቶ ውሳኔ እንዲያሳልፍ ከማድረግ በተጨማሪ በህዝብ ስም የዓለም

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶችና መንግስታት እንዲያውቁት ለማድረግ ልዩ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራ ለመግባት ዝግጅት ላይ ነን::

ፍኖተ ነፃነት፡- ዜጎች ለምን እንዲፈናቀሉ እንደሚደረግስ የደረሳችሁበት ጥናት አለ?

አቶ ሙላት፡- አንዳንዱን በልማት ስም ነዋሪውን ከቀዬው እንዲነሳና የኢኮኖሚ ጥገኛ እንዲሆን ለማድረግ ሲባል እንደሆነ እና አንዳንዱን ደግሞ ያለምንም ምክንያት አንዱን ማኅበረሰብ በሌላው ላይ ጥላቻ በመንዛት ለፖለቲካ ትርፍና ለስልጣን ሲባል እንደሚፈፀም ይታወቃል:: ይሁን እንጂ ዜጎችን በማፈናቀል የሚመጣ ትርፍ የለም::

ፍኖተ ነፃነት፡- በዋነኝነት የኮሚቴው ስራ ምንድነው?

አቶ ሙላት፡- የኮሚቴው አንዱ ቡድን ጉዳዩ ህገወጥ ተግባር መሆኑን በመግለፅ ለህጋዊ እርምጃ እንዲመች በሀገር ውስጥና በመላው ዓለም ላሉ ኢትዮጵያዊያን የዓለማው ደጋፊዎች የተዘጋጀውን ፒቲሽን እንዲፈርሙ ማድረግ ሲሆን ሌላው በጉዳዩ ዙሪያ ከምሁራን ጋር በሀገር አቀፍ ደረጃ የፓናል ውይይት እንዲካሄድ ማመቻቸት፣ ወንጀለኞች እንዴት በህግ ተጠያቂ ማድረግ እንደሚቻል በርካታ የህግ ስራዎችን ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር በመምከር ወደ ተግባር እንዲገባ የሚያደርግ ኮሚቴ ነው::

ፍኖተ ነፃነት፡- በአሁን ወቅት ከጥናት ባለፈ አንድነት ፓርቲ በተፈናቃዮች ዙሪያ የያዘው ወጥ አቋም ምንድነው?

አቶ ሙላት፡- አሁን በሀገራችን ላይ እየተካሄደ ያለው ዜጎችን የማፈናቀል ስራ ህገወጥ ነው ብሎ ያምናል፤ ማመን ብቻም አይደለም በህግ ሊጠየቁም ይገባል የሚል ወጥ አቋም ነው ያለን:: ምክንያቱም አንድነት ፓርቲ የቆመለት ዋነኛ ዓላማ አንዱ ዜጎች በሀገራቸው በነፃነት የመኖር፣ የመስራትና የመጠቀም መብታቸው እንዲከበር ማድረግ ነው:: ይሄ የፖለቲካ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የዜጎች በህይወት የመኖር ያለመኖር የህልውና ጉዳይም ጭምር ነው::

ፍኖተ ነፃነት፡- የተዋቀረው ኮሚቴ ስራውን መቼ ጀምሮ መቼ ያጠናቅቃል?

አቶ ሙላት፡- በርግጥ እንደፓርቲው አቋምና ዕቅድ ከሆነ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት ተብሎ ታስቧል:: ነገር ግን ጉዳዩ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ስለሆነ ዛሬ ካላቆምነው ነገ በሁሉም ስፍራና ማኀበረሰብ የማፈናቀሉ ስራ ሊቀጥል ስለሚችል ሌሎች የዴሞክራሶያዊ ኃይሎች በተለይም 33 ፒቲሽን ፈራሚ ፓርቲዎች ጋርም ጉዳዩን በመውሰድ መመካከርና መወሰን ስላለብን በአሁን ሰዓት ትክክለኛውን ቀን ልነግርህ አልችልም::

ምክንያቱም 33ቱ ፓርቲዎች ጋር ደርሶ ምክክሩ ተጠናቆ ለውሳኔ አልደረሰምና:: ነገር ግን ከዚህ ውሳኔ በኋላ ትክክለኛ የስራው ትግበራና ፍፃሜ ስለሚታወቅ ያኔ በመገናኛ ብዙኃን ለህዝቡ ይፋ እናደርጋለን::

ፍኖተ ነፃነት፡- በመጨረሻ ወደህግ አምርታችሁ ውጤት ባይገኝስ ምን ለማድረግ አስባችኋል?

አቶ ሙላት፡- ኢህአዴግ እራሱ ባወጣው ህግ በህዝቡ እንዲገደድ ለማድረግ ከወዲሁ ጥናቶች እየተሰሩ ሲሆን በመጨረሻ በምንም መልኩ ከሰሩት ወንጀል ሊያመልጡ ስለማይችሉ ለህዝባዊ ውሳኔ እናቀርባለን:: ይህ የሚሆነው ግን ኢህአዴግ እራሱ ባወጣው ህግ አልጠየቅም በሚል ልክ እስካሁን እንደፈፀማቸው የህግ ስህተቶች የሚቀጥልበት ዕድል ሊኖረው አይችልም:: አሁን ያለንበት ጊዜ በሀገርና በህዝብ ላይ ወንጀል ሲፈፀም ዝም ብለን የምናይበትና በጋዜጣዊ መግለጫ ብቻ ተቃውሞ በማቅረብ የምንቀጥል አይሆንም:: ምክንያቱም በሀገርና በህዝብ ላይ ጥፋት እየተፈፀመ በዝምታ ማለፍና ከንፈር መምጠጥ መፍትሄ እንደማይሆን ስላየን በምንከተለው ህጋዊና ሰላማዊ የትግል ስልት የተለያዩ አስገዳጅ ተግባራትን ለመፈፀም ተዘጋጅተናል:: ይህም ወንጀለኞን ለፍርድ ከማቅረብ በተጨማሪ እስከ ፖለቲካዊ ውሳኔ ሊያስኬደን ይችላል::

ፍኖተ ነፃነት፡- በመጨረሻ ለመናገር ፈልገው ይኽ ቀረ የሚሉት ካለ ዕድሉን ልስጦት::

አቶ ሙላት፡- በዚህች ሀገር ላይ ያሉ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በሀገራቸውና በንብረታቸው ጉዳይ በነፃነት እንዲወስኑ ቆርጠው በመነሳት ማንኛም ኢትዮጵያዊ ሲፈናቀልም ሆነ ሊፈናቀል ሲል ለምን ብሎ በመጠየቅ የነበረ የድሮ አንድነታችን እንዲቀጥልና በእያንዳንዱ ላይ የሚፈፀም ጥቃት እንዲቆም ዛሬም በአንድነት ድርጊቱ በማውገዝ የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል:: ይህን ስል ሁላችንም ኢትዮጵያዊያን እንደመሆናችን መጠን የአንዱ ችግር ነገ በሌላውም ላይ መድረሱ ስለማይቀር እንዲህ ዓይነቱን ዜጎንን የማፈናቀል ተግባር እንዲቆም በጋራ መታገል ስለሚያስፈልግ ከጎናችን በመቆም ያሰብነው እንዲሳካ የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉልን እጠይቃለሁ:: ሌላው የዴሞክራሲ ኃይል የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችም በብሔርም ይሁን ህብረብሔር ይመስረት ማንኛውም ዜጋ ሲፈናቀል ሁላችንም ሳንነጣጠል በጋራ በማውገዝ ድርጊቱ እንዲቆም ከማድረግ በተጨማሪ በሀገራችን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት እንዲመሰረት በጋራ ልንቀሳቀስ ይገባል:: እዚህ ላይ የሚመለከታቸው ባለሙያዎችም አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርጉልን ይገባል እላለሁ::

> **የዚህም ድርጊት ፈፃሚ እራሱ ኢህአዴግ ሆን ብሎ ለስልጣኑ መራዘም የተጠቀመበት ኃላፊነት የጎደለው ስራ መሆኑንም የጥናት ውጤቶቻችን ያስረዳሉ:: ይህንንም መሰረት በማድረግ አንድነት ዝም ብሎ መግለጫ ከማውጣት ባለፈ ወንጀለኞች በህግ እንዲጠየቁና መላው የሀገሪቱ ህዝብ በጉዳዩ ዙሪያ ተወያይቶ ውሳኔ እንዲያሳልፍ ከማድረግ በተጨማሪ በህዝብ ስም የዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶችና መንግስታት እንዲያውቁት ለማድረግ ልዩ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራ ለመግባት ዝግጅት ላይ ነን::**

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# የመድረክ ውህደትም ሆነ መፍረስ የአንድነት ቀዳሚ አጀንዳ አይደለም

አቶ ተክሌ በቀለ



አቶ ተክሌ በቀለ

## መግቢያ

ሰንደቅ ጋዜጣ በአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ላይ ከቀስት ወርዋሪዎች መሃል አንዷ መሆኗ ለምንነት ባይረዳኝም ረቡዕ ሚያዚያ 23/2005 ዓ.ም ይዛ የወጣችው ዘገባ ግን የጋዜጣዋ ችግር አይደለም፡፡ አንድነትን ከህዝብና ከደጋፊው ለማጣላት ሚዛናዊ ያልሆነና ያልተጣራ ዘገባ የሰራችበትን ‘’የኪራይ ሰብሳቢነት ትንታኔ በአንድነት’’ አይነት ሳይሆን ይሄኛው ዘገባዋ እውነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዘገባውም በላይ የአንድነት/መድረክ አጠቃላይ አመራርና የግንኙነት ሁኔታን ሳይሆን በዘገባው የተካተቱትን መሪዎች ማንነት በማጋለጥ በኩል የበኩሏን አስተዋፅኦ አድርጋለች፡፡ በዚህም መነሻ የተሰማኝን የግሌን አስተያየት ለመስጠት ይህን ፅሁፍ አዘጋጀሁ፡፡

በመሰረቱ የአንድ ፓርቲ የአመራርና የሚከተለው በፕሮግራም የተደገፈ እምነት እንዲሁም የሚመራበት ደንብ ከውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ጋር እየተጣጣመ እንዲሄድ ተለዋዋጭ እና አዳጊ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለአወንታዊ ለውጥ ዝግጁ መሆንም ይኖርበታል፡፡ የፖለቲካ ትኩሳት በሚለበልባት ኢትዮጵያችን የተለያየ ፍላጎት ያላቸውን ቡድኖችን ማስተናገድ የሚችል የጋራ ደንብና ፕሮግራም ይኖር ዘንድ ሁኔታዎች ያስገድዳሉ፡፡

የግለሰብ እና የቡድን ዴሞክራሲ ሳይዛባ ከተከበረ የማይፈታ ፍላጎት እስከሌለ ድረስ ቡድኖች ፍፁም ዴሞክራሲያዊያን ከሆኑ አብሮ ከመስራት የሚያግድ ነገር አይኖርም፡፡ ከዚህ መሰረታዊ እምነት በመነሳት በህብረ ብሄርና በብሄር የተደራጁ ሀይሎች በኢትዮጵያችን ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በመድረክ ስር ተሰባስበዋል፡፡

ስብስቡ በከባድ ወከባ ውስጥ ሆኖም ከፍተኛ የፖለቲካ ጥቅሞች ያገኘውን ያህል የሚጠበቅበትን ርቀት እንዳልተጓዘ ግን የበርካታ ወገኖች ትችት ሆኖ ይገኛል፡፡ የበለጠ መጠናከር ይቻለው ዘንድ ያባል ፓርቲዎችና የደጋፊዎችን መቅን በማጎልበት ንቅናቄ መፍጠር ወሳኝነት ጎልቶ ይታያል ፡፡ በመሆኑም ነው አንድነት እንደ ፓርቲ ጉዳዩ አሳስቦት በብሄራዊ ምክር ቤት ላለፈው አንድ አመት ሙሉ ሲነሳ ሲወርድ ቆይቶ መጋቢት 14/2005 ባካሄደው ስብሰባ አምስት አባለላት ያሉት ኮሚቴ በመሰየም ችግሩን በዳሰሳ መልክ አቅርቦ የውይይት መነሻ የሚሆን ሃሳብ እንዲያቀርብ ያዘዘው፡፡ ኮሚቴውም በአጭር ጊዜ ስራውን አጠናቆ ሚያዚያ 19 ቀን 2005 ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ በዚህ የመነሻ ሃሳብ መነሻነት ከፍተኛ ውይይት ከተካሄደ በኋላ ሰነዱ በምክር ቤቱ የተሰጡትን ግብአቶች በማካተት በአንድ ሳምንት ውስጥ ለስራ አስፈፃሚ እንዲቀርብና፣ ለመድረክና ለአባል ፓርቲዎች በብሄራዊ ስራ አስፈፃሚው በኩል ቀርቦ ውይይት እንዲካሄድበት፣ ለህዝብም ክፍት የሆነ ሰነድ እንዲሆን ወስኗል፡፡ በመጨረሻም ያለውን የእድገት ለውጥ ስራ አስፈፃሚው በሶስት ወር ጊዜ ለብሄራዊ ምክር ቤቱ እንዲያቀርብና የፓርቲዎቹን ግንኙነት ለሚወስነው የጠቅላላ የጉባኤ አካል በሚቀጥለው ስብሰባ እንዲቀርብለት የሚል ሂደቱን የጠበቀ ውሳኔ ተላልፏል፡፡ ይህም ተገቢና ዴሞክራሲያዊ አሰራር ነው፡፡

### በሂደት የታዩ ግድፈቶች-በአንድነት

የአንድነት ብሄራዊ ምክር ቤት የሰየመው ኮሚቴ የዳሰሳ ስራውን ለውይይት መነሻ እንዲሆንና ከውይይቱ የሚገኙትን ግብዓቶች በማካተት ሙሉ ሰነድ እንዲዘጋጅ ነው፡፡ ለመድረክና ለአባል ፓርቲዎች በውስጥ አሰራራችን መሰረት በስራ አስፈፃሚ በኩል እንዲቀርብና ይህም ለአባላት ፣ ለደጋፊው ህዝብ ይፋ እንዲደረግ የሚል ነበር፡፡ የኮሚቴው አባላት ሰነዱን ለሌላ ወገን የማስራጨትና ስለ ሰነዱም መግለጫም ማብራሪያም የመስጠት ስልጣን አልተሰጣቸውም፡፡ እዚህ ላይ የተፈጠረውን ቴክኒካል ስህተት በምን ሁኔታ እደሆነ አንድነት በውስጡ ያየዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ አቶ ሃብታሙ አያሌውን እዚህ ቦታ አስገብቶ ከመድረክ ጋር እንዲፋጠጥ የተደረገበትን ተግባር ግን ከዚህም በላይ ልናየው ይገባል፡፡ ከውስጥ ነገሩ ሳይታያቸው የሚያቀባብሉ ሰዎችና የጋዜጣው ሚና መንገድ ላይ ተገናኝተው ፓርቲው ውስጥ ነገር ለመቆስቆስ የታሰበበትን ሁኔታ የአንድነት ሰዎች ብቻ የሚተው ሳይሆን የመድረክ ደጋፊዎችና ታጋዮች በአፅዕኖት ልንመረምረው ይገባል፡፡ አቶ ሃብታሙ የሰጣቸው አስተያየቶች እውነትም ስሜትም ያሉበትን ያክል መድረክን ካለበት ፍዘት የሚያነቃ እንጂ የሚያፈርስ ተደርጎ መታየት አለበት ብዬ አላምንም፡፡ መድረክ የእንቧይ ካብ አይደለምና ጠንካራ ፓርቲን ማየት የማይመኙ ምኞት ብቻ ይሆናል፡፡ መድረክ አሁን ካለበት ሁኔታ በይዘትም በቅርፅም ይለወጥ ዘንድ መስራት ግን የመድረክ አባላት ግዴታ የሆነበት ወቅት ላይ ነን፡፡ ያለንበት ሁኔታ ከስሜትና ከፓርቲ ስልጣን በላይ መሆኑ ለሁላችን ሚስጥር ነው ማለት ሊሆን አይችልም፡፡

### የመድረክ አመራሮችና ምላሻቸው

የጋዜጣው ዘጋቢ አቶ ሃብታሙ አያሌው ለሰጡት ቃለ ምልልስ በሚዛናዊነት መልስ እንዲሰጡ የጠየቀው የወቅቱን የመድረክ ሊቀመንበር አቶ ጥላሁን እንደሻው፣ የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ (ኦህኮ) ሊቀመንበር ዶ/ር መራራ ጉዲናንና የአረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ሉአላዊነት /አረና/ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አስራትን ነው፡፡ የአንዱ ፓርቲ መሪ አልተካተቱም ፡፡ እነዚህ አመራሮች ከአቶ ሃብታሙ አያሌው በላይ የፖለቲካ አመራር ልምድ ያላቸውና በተቃውሞ ጎራም ከፍተኛ ዋጋ እየከፈሉ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ናቸው፡፡ ሁሉም ሰነዱ እንዳልደረሳቸው የተናገሩ ሲሆን መረጃውን ወይ ወሬውን የሰሙት በተባራሪ ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የሰጡት ምላሽ ግን የተለያየ ነው፡፡ በኔ አተያይ ፍፁም ዲሞክራሲያዊና ኢዲሞክራሲያዊ የሆኑ መልሶች ነበሩ፡፡

በኢትዮጵያዊያን ዘንድ የተለየ ክብር ያላቸው እና አንዲትም ሳንቲም ለግላቸው ከኢትዮጵያዊያን ያልወሰዱት አቶ ገብሩ አስራት እራሳቸውን፣ መድረክን እና ፓርቲያቸውን የሚመጥን መልስ ሰተዋል፡፡ አንድ ፓርቲ እራሱን ብቻ ሳይሆን በግንባርነት የተቀላቀለውን ሌላ ፓርቲ የመገምገም፣ የውስጥ ለውጥ ይኖር ዘንድ የመጠየቅ፣ እምነቱን በነፃነት የማራመድ ሙሉ መብት አለው፡፡ እውነት ነው ይህ ወንጀል አይሆንም፡፡

መድረክ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የግንባሮች ስብስብ እንጂ ታቦት አይደለም፡፡ ይነካል፣ ይገመገማል፣ ይሻሻል ዘንድ

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

ይጠየቃል:: ጥያቄ ማንሳት፣ መድረክን መገምገም፣ አመራሩንም መወጠር ከመድረክ መፍረስ ጋር አይያያዝም:: መድረክ ይበልጥ መጠናከር እንዳለበት ሁሉን የሚያስማማ ቢሆንም የወቅቱን ሁናቴ የሚመጥን ፓርቲና ተሰባሪ ሸክላ አለመሆኑን አስረግጠው በመናገራቸው ሊመሰገኑ ይገባል::

ዶ/ር መራራ ጉዲና የተናገሩት የፓርቲያቸውን /ሁለቱን/ አቋም እንደማይወክል እርግጠኛ መሆን ይቻላል:: የወረወሯቸው ያልተመጠኑ ቃላት እራሳቸውን እንጂ በሚመሩት ስብስብ ውስጥ ያሉትን የፓርቲ አመራሮችን አይመለከትም:: የኢትዮጵያ ችግር ከብሄርና ከህብረብሄር ችግር በላይ መሆኑን እንደ አዲስ ሊያስተምሩን ይሞክራሉ:: የጠቃቀሱት ምሳሌ ሁሉ ከመድረክ ሁኔታ ሲመዘን አብሮ የማይሄድ የአካዳሚክ ወሬ ነው:: የጀርመንና የእስራኤልን የአገርነት ሁኔታ ፣ የነዚህ አገሮች ፓርቲዎች ያሉበት እድገት እና የመድረክ ሃገራችን ውስጣዊና ውጫዊ ከባቢያዊ ሁናቴ አራንባና ቆቦ መሆኑን መረዳት ያቃተው ፖለቲከኛ መድረክ ውስጥ መኖር አልነበረበትም:: ከሁሉም የሚገርመው "አሁንም ኢህአዴግ ከሚቀልባቸው ሰዎች የሚነሳ ጥያቄ እንጂ ችግሩ የፖለቲካ ፕሮግራም አይደለም" ብለው የሚደመድሙት እሳቤ ነው:: ከተቃውሞ ጎራ ወደ ኢህአዴግ መግባትና ከኢህአዴግም ወደ ተቃውሞ ሰፈር መግባት የግለሰብ መብትና እምነት በመሆኑ ሊከበሩ ይገባል:: አቋማችንን ደግፈው የሚቀላቀሉን ቄጤማውን እረግጠው የመጡ የህዝብ ልጆች የመሰላቸውን ጥያቄ ለማንሳት የመሪዎችን ቡራኬ መጠበቅ የለባቸውም:: ጥላን እየጠረጠሩ እየፈሩ መኖር የሚቻልበት ጊዜ ላይ አይደለንም:: የለውጥ ፈለጊ ታጋዮችን የኢህአዴግ ካባ እየደረቡ ለማሸማቀቅ መሞከር ጊዜው አልፎበታልና ሊታረም ይገባል የሚል እምነት አለኝ::

ወደ አቶ ጥላሁን እንደሻው ልግባ:: እኚህ ታጋይ መድረኩ በዙር የደረሳቸው መሪ ናቸው:: አንድነት መድረክ የግምገማ ሪፖርት ላይ ለጋዜጣው የሰጡት ምላሽም የአቅማቸውን ነው:: የአንድነት ምክር ቤት ውሳኔን አሳንሰው ሲያበቁ "የአንድነት የውስጥ ክርክር እንጂ እኛን የሚመለከት አይደለም" ብለውታል:: ተመስገን ደሳለኝ ከዚህ በፊት መድረክን ከአፍሪካ ህብረት ጋር ያነፃፀረበትን እውነታ ደግፈውታል:: አንድነት ግን የመድረክ አባላቶች ጉዳይም በጣም ያስጨንቀዋል:: በሙሉ ቁመና ያሉት /ስራ አስፈፃሚና ማዕከላዊ ኮሚቴ ኑሮአቸው ህገ ደንባቸው በሚፈቅደው መሰረት ስብሰባዎችን በማካሄድ ውሳኔ የሚያስተላልፉ/ ቀርቶ ለስም መጠሪያነት ያሉትም ያሳስበዋል:: እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት የጠቅላይነት ባህሪ ስላለው ሳይሆን የኢትዮጵያ ችግር በአንድ የፖለቲካ ቡድን ይፈታል ብሎ ባለማወላወል ስለማያምን ነው:: ተግባሩም ስሙን እንዲመስል ዋጋም እየከፈለ እየታገለ የመጣ ፓርቲ ነው::

የአንድነት ስራ አስፈፃሚና የብሄራዊ ምክር ቤት እራሳቸውን የሚገመግሙ፣ ደንብና ፕሮግራሙን የሚያከብሩ፣ ለህዝብና ለአገር ሌት ተቀን የሚሰሩ ህልውና ያላቸው የተለያዩ የፓርቲው ዲሞክራሲያዊ ተቋማት ናቸው:: ህገ ወጥ ግምገማ አላደረጉም:: መድረክን መገምገም ሙሉ መብትና ስልጣን አላቸው:: መድረክ መገምገም አለበት ብሎ ብሄራዊ ምክር ቤት መጠየቁ ተማሪው ከመምህሩ መብለጡን ያሳያል:: አንድነት ወደ መድረክ ተጋብዞ የመጣ የኗላ እንግዳና ተማሪ መሆኑን በባለቤትነት ስሜት ሊነግሩን ሞክረዋል- አቶ ጥላሁን እንደሻው:: በመድረክ ጉዳይ ላይ አንድነት የውስጥ ትግል የለበትም:: ቢኖርም ዲሞክራሲያዊ እና ተፈጥሮአዊ ነው:: ሁሉንም አባል በቁጭት የሚያንገበግበው ግን ትግሉ ከሚጠይቀው ፍጥነት አንፃር የመድረክ ዝግታ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል:: የአንድነት ግምገማ ግን አንድነት ለመድረክ ፍዘት ያበረከተዉ አሉታዊ አበርክቶ ካለውም የድርሻውን ለማንሳት ገምግሞ ሰነዱ ላይ እንዲካተት ውሳኔ ሰጥትቶበታል::

> **ስብስቡ በከባድ ወከባ ውስጥ ሆኖም ከፍተኛ የፖለቲካ ጥቅሞች የያገኘውን ያህል የሚጠበቅበትን ርቀት እንዳልተጓዘ ግን የበርካታ ወገኖች ትችት ሆኖ ይገኛል:: የበለጠ መጠናከር ይቻለዉ ዘንድ ያባል ፓርቲዎችና የደጋፊዎችን መቅን በማጎልበት ንቅናቄ መፍጠር ወሳኝነት ጎልቶ ይታያል ::**

## መደምደሚያ

የአንድነት ብሄራዊ ምክር ቤት ለመድረክና ለአባል ፓርቲዎቹ የሚያቀርበው ለህዝብ ክፍት የሆነ ሰነድ ለውይይት መነሻ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ:: የኮሚቴው ግኝት ሳይሆን በግሌ የመድረክ መተዳደሪያ ደንብ ኢዲሞክራሲያዊ እና ሌሎች እንዳይገቡ ዘጊም ነው የሚል አቋም አለኝ:: ጉዳዩ ያገባኛል የሚል ወገን ሊመለከተው ይገባል:: የመድረክ አባል ፓርቲዎችና የመድረኩ አመራር ዲሞክራሲያዊ አይደሉም ብዬ ግን አላምንም:: ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ ደንብ ዲሞክራሲያዊ አመራርን ከርምጃው ሊገታው እንደሚችል ይታመናል:: የዲሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብ የሚፈታተናቸው ችግር ያለባቸው የመድረኩ አመራር አባላት ሊኖሩ እንደሚችሉ ግን ከመግለፅ አልቆጠብም:: የመድረኩ አባል ፓርቲዎች ዲሞክራሲያዊና ስልጡን በሆነ አካሄድ ራሳቸውን ፈትሸው፣ በጠቅላላ ጉባኤያቸውም አስወስነው ዘላቂና አገራዊ ሃላፊነትን መሸከም የሚችል ጠንካራ መድረክን በመፍጠሩ ሂደት በቁርጠኝነት ይሰራሉ የሚል እምነትና ምኞት አለኝ:: ይህ እስኪሆን ሁሉም በየፓርቲው በሃላፊነት ስሜት ሊታገል ይገባል:: በሁሉም ወገን ያልበሰለን እና ያላለቀን ሃሳብ እያንጠለጠሉ ወደ ሚዲያ ማውጣት ግን የሰለጠነ አስተሳሰብ መገለጫ አይደለም:: በህዝብ፣ በደጋፊና አባላት ዘንድ ጥርጣሬን ከመፍጠር ባሻገር ትዝብት ላይ ይጥላል:: ከኢህአዴግ የምንማረው ምንም ነገር የለም ብሎ መዘጋት የሚቻል አይመስለኝም:: ልናስተዳድር እየታገልን ያለነው ከፍተኛ ችግር ውስጥ ያለችዉን ሀገር ኢትዮጵያን ነው:: የመድረክ ውህደትም ሆነ መፍረስ የአንድነት ቀዳሚ አጀንዳ አይደለም:: ከገዥው ግንባር በተሻለ እውነተኛና ህይወት ያለው ግንባር መፍጠር ከዚያም ሲያልፍ የተፋጠነ ውህደትን ማየት ግን የህዝብ ወቅታዊ ጥያቄ ነው የሚል ሀሳብ ይሰማኛል:: ሁላችንም ልንመልሰው የሚገባን አንገብጋቢ ጥያቄም ይመስለኛል::

**ቸር እንሰንብት!!**

**አቶ ተክሌ በቀለ የአንድነት የብሄራዊ ስራ አስፈፃሚ አባል ናቸው**

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# መንግስት በህገ ወጥ እስር ቤቶችን ዜጎችን እያሰቃየ ነው

ህውሃት/ኢህአዴግ/ አገሪቱን በመሳሪያ ሀይል ተቆጣጥሮ ማስተዳደር ከጀመረ 22 ዓመት ያስቆጠረ ቢሆንም ዛሬም በህገ ወጥ እስር ቤቶች እየተገለገለ ስለሆነ እስር ቤቱን እንዲዘጋ አንዳንድ የአገሪቱ ዜጎች ጥሪ እያቀረቡ ነው፡፡

ጥሪው የቀረበው ሰሞኑን የህውሀት መስራች እና በአሁን ጊዜ የአረና ፓርቲ ከፍተኛ አመራር የሆኑት የአቶ አስገደ ገ/ሥላሴ ልጅ በህገ ወጥ እስር ቤት እንደታሠረ ከተሠማ በኋላ ነው፡፡

የመረጃ ምንጮቻችን እንደሚሉት "ህውሃት" በጫካ በነበረበት ወቅት ባዶ 6 በሚል መጠሪያ በየቦታው እስር ቤቶችን አቋቁሞ ዓለም አቀፍ የእስረኛ አያያዝን በሚያሟላ መንገድ እስረኞችን ያስር ነበር፡፡
በየ እስር ቤቶች ቶርችና ግድያ ይፈፀም ነበር፡፡ መንግስት ከሆነም በኋላ ማሰቃየት የሚፈልጋቸውን ሰዎችና በቶርች መረጃዎችን ለማግኘት ሲባል እነዚህን እስር ቤቶች ይጠቀማል ብለዋል፡፡ ቅሬታ አቅራቢዎቹ በማያያዝም "በቅርቡ የአቶ አስገዳ ልጅ የአባትህን ጹሑፍ በኢንተርኔት ታስረጫለህ በሚል ከተያዘ በኋላ ከህጋዊ እስር ቤት አውጥተው ባዶ 6 ወደሚባል ህገወጥ እስር ቤት መዛወሩን አባቱ ይፋ አድርገዋል፡፡

"መንግስት እንደመንግስት ኃላፊነት ሊሰማው ይገባዋል፡፡ ከህገወጥ ተግባር መታቀብ አለበት፡፡ ስለዚህ በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን ህገወጥ እስር ቤቶችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መዝጋት አለበት፡፡" ካሉ በኋላ የኢህአዴግ መንግስት ከዚህ ድርጅቱ እንዲቆጠብ ጥሪያችን አስተላልፉልን ሲሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

# ቂሊንጦ የሚገኙ እስረኞች ወደ ዝዋይ እየተወሰዱ ናቸው

በሽብርተኝነት ተከሰው የተፈረደባቸው እና በይግባኝ ክርክር ላይ የሚገኙ የነበሩት ፖለቲከኞች ከቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ወደ ዝዋይ ማረሚያ ቤት እየተወሰዱ መሆኑን ቤተሠቦቻቸው ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ፡፡

የእስረኛ ቤተሠቦች እንደሚሉት "የጠየቁት የይግባኝ ክርክር ውሳኔ ሳያገኝ እና እንዲሁም ቤተሠቦቻቸው በሚገኙበት አካባቢ መታሠር ሲገባቸው እስረኞቹን ወደ ዝዋይ መዘዋወራቸው እጅግ አሣዝኗል፡፡ ሲሉ ቅሬታቸውን ገልጸዋል፡፡ የቀድሞ የፓርላማ አባል የነበሩት እና ከፓርላማው በክብር ተሸኝተው በሀገሪቱ ውስጥ ሠርተው መኖር ባለመቻላቸው በስደት ወደ ሱዳን ከሄዱ በኋላ ታስረው የተመለሱት አቶ አንዱአለም አያሌው ከአንድነት ፖርቲን ወክለው ለፓርላማ የተወዳደሩት ሻምበል የሽዋስ ይሁንአለም እና በሽብርተኝነት ተከሠው በእስር ላይ የሚገኙት አቶ ምትኩ ዳምጤን ጨምሮ ከ100 በላይ እስረኞች ከቂሊንጦ ወደ ዝዋይ ተጓጉዘዋል፡፡ እስረኞቹ በሌሉበት የይግባኝ አቤቱታቸውን የተመለከተ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሀል ዳኛ አቶ ዳኜ መላኩ እስረኞቹ ያልቀረቡበትን ምክንያት ጠይቀው ወደ ዝዋይ በመሄዳቸው ምክንያት እንደሆነ ሲነገራቸው ክርክሩ ሳያልቅ እንዳይሄዱ ብለን ነበር ለምን ሄዱ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ይሁን እንጅ የማረሚያ ቤቱ ተወካይ አሣማኝ እና በቂ መልስ መስጠት አልቻሉም ፡፡ በቅርቡ ጋዜጠኛ ውብሸት ታየ ከቂሊንጦ ወደ ዝዋይ እስር ቤት መዛወሩ ይታወቃል፡፡

# በቡሌ ሆራ የሚትገኘው ቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን እንዲፈርስ መታዘዙ ቁጣን ቀሰቀሰ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ቦረና ዞን ቡሌ ሆራ/ ሀገረ ማርያም/ ከተማ የምትገኘው ቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን እንዲፈርስ መታዘዙ በአካባቢው ቁጣ መቀስቀሱን ታወቀ፡፡

የአካባቢው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት ተከታዮች ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት "የከተማው ከንቲባ ሀላፊነት በጎደለው እና በማን አለብኝነት ቤተክርስቲያኑን አፍርሰው ቦታውን ለባለሀብት ለመሸጥ መወሰናቸው ለሀይማኖቱም ለህዝቡም ያላቸውን ንቀት ያሳዩበት ነው፡፡" ሲሉ አውግዘዋል፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች አሁን የወሰዱትን አቋም ሲገልጹ የከተማው ከንቲባ በድፍረት ቤተክርስቲያኑን አፍርሰን እንጨትና ቆርቆቆውን እንድናነሳ አዘዋል ፡፡
"እኛ የእግዚያብሄርን ቤት አናፈርስም ፡፡ እሳቸው ከፈለጉበት በሚረፈልጉት ኃይል ሊያስፈርሱ ይችላሉ ፡፡ ለወረዳው አስተዳደር አመልክተን የወረዳው አስተዳዳሪ በስፍራው ተገኝተውተ ተመልክተውታል ፡፡ ቤተክርስቲያኑ እንዳይፈርስ የሚያስችለው ውሳኔ ይሰጣሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን" ሲሉ ተናግረተዋል ፡፡
አስተያየት ሰጪዎቹ በመጨረሻ በሰጡት አስተያየት በዚሁ ከተማ የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን አለ፡፡ ይህ ቤተ ክርስቲያን ካለፈው መንግስት ጀምሮ በከተማው ማስተርፕላን መሰረት ፍቃድና ካርታ አለው ይሁን እንጂ እኚህ የከተማው ከንቲባ ቦታውንና ከቦታው ላይ ያለውን ባህርዛፍ አላስረክብም ብለው ችግር ፈጥረውብን እስካሁን ችግሩ ባልተታበት ሁኔታ እንደገና አሁን ደግሞ ፊታቸውን ወደ ቅድስት አርሴማ ማዘወራቸው ገርሞናል ብለዋል ከተማውን ከንቲባ አቶ ቡሌ ገመዳ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት በተንቀሳቃሽ ስልካቸው እና በጽ/ቤታቸው ስልክ ለማግኘት ያደረግነው መከራ ለጊዜው አልተሳካም ፡፡

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# አንድነት ፓርቲ ማተሚያ ማሽን በመግዛት የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ህትመት ለማስቀጠል የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀግብር ጀምሯል

እርስዎም :-

. ኩፖን በመግዛት

. የቃልኪዳን ሰነድ በመሙላት

. አቢሲኒያ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ የባንክ ሒሳብ ቁጥር 47 ገቢ በማድረግ አጋርነትዎን ያረጋግጡ

ለተጨማሪ መረጃ

0933-89-17-66 እና

0933-89-17-67 ይደውሉ

udjparty@gmail.com

## ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ወደ ህትመት እንድትመለስ በመርዳት መረጃ የማግኘት መብትዎን ያስከብሩ!!

ፍኖተ ነፃነት

የኢትዮጵያን ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

## አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67